# ተናገር መቃብር

(ከእጅጉ ረታ ዓለሙ )

ተጠየቅ መቃብር፡

        የምትመልስ ቢሆን

ወይም ምናገባህ

        የምትለኝ ባይሆን፧

ሆድህ የማይሞላ

        ከርሳም ነህ ይሉሐል

ሕጻን ሽማግሌ

        ወንድ ሴት የማትል

ትንሹን ትልቁን

        የምታግተለትል።

እስቲ ዘክዝክልኝ

        ንገረኝ መቃብር

አንድም ሳትደብቀኝ

        የሆድህን ሚስጥር።

እስቲ ልጠይቅህ

የሚሄዱት ሁሉ እንዲያ እንዲያ ሆነው

        የት ነው መኖርያቸው?

        ምንድን ነው ሥራቸው?

እስቲ ልጠይቅህ እኒያ……

የምስር የኑብያ ኃያላን ነገሥታት

የፒራሚድ ጎጆ ቀልሰው ያገቡት

wwwethiopianorthodox.org

እንዴት ያምራሉ?

ምንስ ይሰራሉ?

የጥንቱ ኃያላን

እኒያ .........እኒያ

የታወቁት በጣም

ዓለም ተንቀጥቅጦ

እንደ ወረቅ እንደ ሰም

እንደቅቤ ቀልጦ

የተገዛላቸዉ

እንዴት ነው ኑሯአቸው?

ምንድን ነው ግብራቸው?

አውጋን እስኪ እንስማ

ጦርነት ነው ሰላም ያሉበት ከተማ፡፡

እስቲ ልጠይቅህ

የሞት መጋረጃ ክልሉ ሲታለፍ

እዚያ ቦታ ያለው

ኑሮው ምን ዓይነት ነው?

እረብሻ ጫጫታ

ድብልቅልቅ ሁካታ

ሐሳብ ውዝዋዜ

ሰቀቀን ትካዜ

ወይስ መልካም እንቅልፍ፡፡

አለ ወይ ጭፈራ

አለወይ ደንካራ

www.ethiopianorthodox.org

አለ ወይ ሽርሽር

ከሚወዷት ጋራ።

        አለ ወይ ሸብሮሌት!

አለ ወይ ፖንቲያክ

አለወይ ካዲላክ

                የሚዘነጥበት ።

ተንኮልና ክፋት

ስስት ምቀኝነት

እርስ በርስ መተማማት

ያለ ካራ ስለት

መቧጨቅ መባላት

በገንዘብ በጉልበት

በስልጣን መመካት፤

        አለወይ ወይ ተናገር

        በሞቴ መቃብር።

ነገር ማንሾካሾክ ፣ ነገር ማመላለስ፤

ሰው ከሰው ማጣላት

        ያውቃሉ ወይ ሙታን

ወዲያ ወዲህ ማለት

                ልጠይቅህ መልስ።

የባርነት ቀንበር የቀለም መከራ

የሚቾች ቁልቁለት የችግር ተራራ፤

        የስቃይ የንዴት

የሐዘን የፀፀት

የረሐብ [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

የማግኘት የማጣት

የመስጠት የመንሳት

ወሬአቸው እንዳለ በሙታን ከተማ ፤

በሞቴ መቃብር ተናገር እንስማ፡፡

ከዚያ የሚገላምጥ

ሰው ባዩኑ የማይሞላ ፤

የሚፈልጥ የሚቆርጥ

ድሐ የሚያጉላላ

ባለ ዘመናይ

በሐብት በስልጣኑ ትምክህት የሚያሳይ

-ሰው ጤፉ

ዝሆን ወፉ -

መቃብር ተናገር ከዚያም አለ ወይ?

ምግብ ከዚያ አለ ወይ?

"ትክን ያለች ዶሮ የጌቶቹ ምሳ

የት አገኛለሁ ወድቄ ብነሳ "

መጠጥ ከዚያ አለወይ?

በድግፍ የሚሄድ

ሁለቱ የሚበቃ፤

የእምብርክክ የሚያስኬድ

ከምድር የሚወቃ፡፡

አሽከር ከዚያ አለወይ?

ቆሞ የሚያገለግል፤

የጣት ውሃ የሚያቀርብ

wwwethiopianorthodox.org

የማግኘት የማጣት

የመስጠት የመንሳት

ወሬአቸው እንዳለ በሙታን ከተማ ፤

በሞቴ መቃብር ተናገር እንስማ።

ከዚያ የሚገላምጥ

ሰው ባዩት የማይሞላ ፤

የሚፈልጥ የሚቆርጥ

ድሐ የሚያጉላላ

ባለ ዘመናይ

በሐብት በስልጣኑ ትምክህት የሚያሳይ

-ሰው ጤፉ

ዝሆን ወፉ -

መቃብር ተናገር ከዚያም አለ ወይ?

ምግብ ከዚያ አለ ወይ?

"ትክን ያለች ዶሮ የጌቶቹ ምሳ

የት አገኝሻለሁ ወድቄ ብነሳ "

መጠጥ ከዚያ አለወይ?

በድግፍ የሚሄድ

ሁለቱ የሚበቃ፤

የእምብርክክ የሚያስኬድ

ከምድር የሚወቃ።

አሽከር ከዚያ አለወይ?

ቆሞ የሚያገለግል፤

የጣት ውሃ የሚያቀርብ

wwwethiopianorthodox.org

ጉርሻ የሚከጅል፡፡

ገረድ ከዚያ አለች ወይ?

እንጨት የምትሰብር ውሃ የምትቀዳ

እንጀራውን ወጡን

ጠጁና ጠላውን

የምታሰናዳ፡፡

እስቲ ልጠይቅህ

በሙታን ባድማ በሙታን ከተማ፤

በርስት መጨቃጨቅ

በመሬት መጣላት

መካሰስ መዋቀስ

በወሰን መጋፋት

የአባቴን የእናቴን

የቅድማያት እርስቴን ይልቀቅልኝ ማለት

አለወይም የለም ተናገር አንስማ፡፡

እስቲ ልጠይቅህ

እነዚያ ሕፃናት

-ምንም የማያውቁት ንጹሐን ፍጥረታት-

እንዴት ይኖራሉ?

ምንስ ያስባሉ?

ጡጦ ወይም ሌላ ፤

ተፈጭቶ ተቦክቶ

ተጋግሮ የሚበላ፡፡

ማሙሽ፤ እሹሩሩ የሚባለው ዜማ፤

wwwethiopianorthodox.org

-የማሙዬን እናት

ቶሎ ነይለት፤

ወተቱን በቡያ

ዳቦውን ባሕያ-

አለ ወይ ተናገር በሙታን ከተማ።

የለቅሶ የሙሾ

ኧረግ-ዋይ-ኧረግ ወይ

መፍረስህ ነው ወይ፤

የደረት መደቃት

ወዮው -ወዮ ማለት

የጸጉር መላጨት

የመውደቅ መነሳት

የለቅሶ ጫጫታ

የሐዘን ጋጋታ

-በመቃብር ዓለም፡-

ታይቶና ተሰምቶ ይታወቃል ወይ?

እስቲ ልጠይቅህ

ጥበብ ከዚያ አለ ወይ

የሕይወት መሠረት

የአዕምሮ መራቀቅ፤

አትኩሮ የማየት

ባሳብ የመጨነቅ

ባየር ላይ የመብረር

በየብስ የመሽከርከር

wwwethiopianorthodox.org

በመርከብ የመስረር

በኤሌክትሮን ፖዎር ምስጢር የመመርመር

ማርስን የመቃኘት ጨረቃን የመዞር

ባውቶሚክ የማቅናት በሀይድሮጅን የማጥፋት

አለወይ ምርምር።

ከዚያ-

የዕፅዋት የአዝርዕት

የዛፍ የቅጠሉ፤

የአትክልት የእንስሳት

የሳር ድንብላሱ።

የሰማይ የምድሩ

የትንሽ ትልቁ፤

ያየር የጠፈሩ

የመዳብ የወርቁ።

የሕመም የበሽታ

የደዌ የሥቃይ፤

የሞትስ መድኃኒት

ይመረመራል ወይ?

አለ ወይ መንሳፈፍ

በእግረ ሕሊና

በጥበብ ምርምር

በእውቀት ጐዳና፤

የቅኔ ቆጠራ

የድርሰት ፈጠራ

የሙዚቃ ቃና

wwwethiopianorthodox.org

የውበት የስዕል

ረቂቅ ፍልሰፍና፡፡

ወይስ ሌላ ዜና-

ምን ታወጋናለህ ስለድንቁርና

ተሸፋፍኖ መኘታ ሃሳብን ጠቅሎ

እስመ ኵሉ ኃላፊ ወርጋፊ ብሎ፡፡

እስቲ ልጠይቅህ

የትኛው ደስ ብሎት በድሎት ይኖራል

የትኛውስ ከፍቶት አንተን ያማርራል፡፡

እባክህ ተናገር

በሞቴ መቃብር፡፡

*1958 ዓ.ም ተጻፈ፡፡*

wwwethiopianorthodox.org